# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 234 ጥቅምት 29 2005 ገጽ 1


**የህሊና እስረኞቹ ፍርደ ገምድል ውሳኔ ሲሰጣቸው ከቶ ሳይደናገጡ ጀግነነት በተሞላበት ለወያኔ ዳኞች የተናገሩት ምላሽ "እናንተ ለምትሰሩት የበደልና ፍርድቤቱን የማዋረድ ስራ ታሪክና ትውልድ ይጠይቃችኋል" በሚል ነው ስለዚህ ሁላችንም ከነዚህ የህሊና እስረኞች ብርታትና ጥንካሬ ብዙ ልንማር እንችላለን። ጀግኖችን በርቱ ማለትም የእኛ ፈንታ ነው።**

ከግንቦት 7 ዕርስ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የቀደሞዉ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ትግራይን የእንዱስትሪ ክልል ለማድረግ ዝግጅት ጨርሰዉ እንደነበር ተሰማ

ሟቹ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የትግራይን ክልል የአገሪቱ የእንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ ዝግጅት ጨርሶ እንደነበርና በአሁኑ ወቅት ባለቤቱ አዜብ መስፍን ይህንኑ በሷ የጀመረዉን የእንዱስትሪ እስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጣ የተነሳች መሆኑን የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። በዚሁ ዘጋቢያችን አዜብ መስፍን በቅርቡ ለዋልታ ኢንፎርሜሺን ማዕከል የሰጠችዉን ቃለመጠይቅ ዋቢ በማድረግ በለከልን ዜና መሰረት መለስ ዜናዊ ትግራይ ዉስጥ ምን አይነት ፋብሪካዎች እንደሚገነቡ፤ ፉት እንደሚገነቡና ለግንባታ የሚወጣዉ ካፒታል ከዬት እንደሚገኝ የሚጠቁም ሰፋ ያለ ጽሁፍ ጽፎ እንደነበር ያስረዳል።

በቅርቡ ከዚህ አለም በሞት ሲለይ "የኢትዮጵያ አባት" ተብሎ የተሞገሰዉና ኢትዮጵያን ሃያ አንድ አመት ሙሉ የመራዉ መለስ ዜናዊ ትግራይን ከዘጠኙ የፌዴራል ክልሎች ነጥሎ የአገሪቱ የእንዱስትሪ ማዕከል ለማድረግ ሰፋ ያለ እስትራቴጂ ነድፎ የማስቀመጡ ዜና ሲሰማ የመለስ ዜናዊን ራዕይ ከግቡ እናደርሳለን ብለዉ የተነሱትን እነ ኃይለማሪያም ደሳለኝን ጨምሮ ብዙ የአገዛዙ አባላት እንደተሸማቀቁ ከአዲስ አበባ የሚደርሱን ዜናዎች ይጠቁማሉ።

አዜብ መስፍን በቅርቡ እሷ እራሷ ከምትመራዉ የኤፎርት ኩባንያዎች አንዱ ለሆነዉ ለዋልታ ኢንፎርሜሺን ማዕከል በሰጠችዉ ቃለ ምልልስ መለስ ዜናዊ ከመሰዋቱ በፊት የአምስት አመት የትግራይ እንዱስትሪ በኤፎርት እንዴት መፈጸም እንዳለበት የፃፈዉ እስትራቴጂ እንደነበር ሳታፍር አፏን ሞልታ ተናግራለች። ኢትዮጵያ ዉስጥ "የሙስናዋ እመቤት" በመባል የምትታወቀዉ አዜብ መስፍን በሷ ለትግራይ የነደፈዉን የእንዱስትሪ እስትራቴጂ በዝርዝር ከመናገሯ ባሻገር እሷና ሌሎችም ብዙ ባለስልጣኖች ይህንን ስትራቴጂ ተግባራዊ ለማድረግ ቀን ከሌት ተግተዉ እንደሚሰሩም ተናግራለች።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የፌዴራል ገቢዎች ባለሥልጣን መ/ቤት የፍትህ ጋዜጣን ንግድ ፈቃድ አላድስም አለ

የፌዴራል ገቢዎች ባለስልጣን መስሪያ ቤት አመታዊ የንግድ ፈቃዳቸዉን ለማደስ የሄዱትን የማስተዋል ህትመትና ማስታወቂያ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የስራ አመራር አባላት የድርጅታቸዉን የንግድ ፈቃድ አላድስም ብሎ እንደመለሳቸዉ የግንቦት 7 ዜና ምንጮች ከአዲስ አበባ በላኩልን ዜና ገለጹ። መስሪያ ቤቱ ለምን ይህንን እርምጃ እንደወሰደ የሰጠዉ ምንም ምክንያት ባይኖርም እርምጃዉ ፍትህ ዝጣን ብሎም ሀሳብን በነፃነት የመግለጽን መብት ለማፈን አገዛዙ ሆን ብሎ የወሰደዉ እርምጃ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ ዘጋቢያችን በየቦታዉ እየተዘዋወረ ያናገራቸዉ ሰዎች በምሬት ተናግረዋል።

በኢትዮጵያዉያን ዘንድ ከፍተኛ ተወዳጅነት የነበራት ፍትህ ጋዜጣ ካለፈዉ ሐምሌ ወር ጀምሮ ህትመቷ እንዲቋረጥ የተደረገ ሲሆን አሁን ደግሞ ጭራሽ ጋዜጣዋን እያሳተመ ለሚያወጣዉ ድርጅት የንግድ ፈቃድ መከልከሉ ከእንግዲህ ፍትህ ጋዜጣ ብቻ ሳትሆን "ፍትህ" እራሷ ሞታለች በማለት ብዙዎች ትችት መሰንዘር ጀምረዋል። ነፃ ሜድያን እንደ ጦር የሚፈራዉ የወያኔ አገዛዝ ባለፉት ስድስት ወራት ፍትህ ጋዜጣን አንዴ በብርሀንና ሠላም ማተሚያ ቤት በኩል፤ ሌላ ግዜ በፍርድ ቤት አሁን ደግሞ በገቢዎች ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በኩል የጥቃት እርምጃ በመዉሰድ አገዛዙ ከአገር ልማትና ጥበቃ በላይ በሙሉ ሀይሉ የተሰማራዉ የዜጎችን መብትና ነፃነት በማፈን ስራዎች ላይ ነዉ ሲሉ አንድ የወያኔ አገዛዝ ሰለቸኝ የሚሉ የፍትህ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለስልጣን ተናገሩ። ኢኚህ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የጠየቁ ባለስልጣን ይህ አስተያየት የእሳቸዉ ብቻ ሳይሆን ብዙዎች አቻዎቻቸዉ የሚጋሩት ሀሳብ መሆኑን ስሜታቸዉን ሳይደብቁ ተናግረዋል።

## አህዴድ ዉስጥ የተፈጠረዉ ክፍፍልና ልዩነት ስር እየሰደደ ነው

ወያኔ ኢትዮጵያን እንዳሻዉ መግዛት እንድችል በአምሳሉ ከፈጠራቸዉ ሦስት ድርጅቶች አንዱ በሆነዉ በኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ዉስጥ በቅርቡ የተካሄደዉን ከፍተኛ የስልጣን ክፍፍል አስመልክቶ የተፈጠረዉ ልዩነት ከፓርቲና ከክልል አልፎ ዞን ደረጃ ላይ የወረደ መሆኑን የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ የኦህዴድ የሚገኙ ዉስጥአዋቂ ምንጮችን ጠቅሶ በላከልን ዜና ገለጸ። ዘጋቢያችን ያናገራቸዉና ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የፈለጉ አንድ ከፍተኛ የኦህዴድ አመራር አባል እንደተናገሩት በድርጅታቸዉ ዉስጥ የተፈጠረዉ መከፋፈል ከላይ ወደታች ወርዶ ኦህዴድ ዉስጥ ሁለት ቡድኖች መፈጠራቸዉን ሳይደብቁ ተናግረዋል። ከተፈጠሩት ሁለት ቡድኖች አንደኛዉ አሁን በስልጣን ላይ የሚገኘዉን የሀይለማሪያም ደሳለኝን መንግስት ተቀብለን እንሂድ የሚል ሲሆን ሁለተኛዉ ቡድን ደግሞ የኦሮሞን ህዝብ ብዛትና ኦህዴድ በኢትዮጵያ ፓርላማ ዉስጥ ያለዉን መቀመጫ ብዛት ከግምት ዉስጥ ባላስገባ መልኩ የተመሰረተዉን የሀይለማሪያም ደሳለኝን መንግስት በፍጹም መቀበል የለብንም ባይ ነዉ።

"ብዙሃኑ በአናሳ አይገዙም" የሚል መፈክር አንግቦ የተነሳዉ ይህ ቡድን ብዙዉን የኢትዮጵያ ህዝብ ለሚወክለዉ ለኦህዴድ የጠ/ሚኒስትርነቱም ሆነ የምክትል ጠ/ሚኒስትርነቱ ቦታ አለመሰጠቱ የሚያመለክተዉ ኦህዴድን በመሳሪያነት ለመጠቀም የሚደረገዉን ጥረት ነዉና በፍጹም አንቀበለዉም ብሏል። በኦህዴድ ዉስጥ የተፈጠረዉ ክፍፍል ስር ሰዶ የሚታየዉ በሀረሪ ክልል ሲሆን ከዚህ በፊት ተነስቶ ያወዛገበዉ "ክልሉን ማን ያስተዳድረዉ" የሚለዉ ጥያቄ አንደገና ማገርሸቱ ታዉቋል።

በኦህዴድ ዉስጥ የተፈጠረዉ ልዩነት በዚህ ከቀጠለ ኦህዴድ በዋናዉ ግንባር በኢህአዴግ ዉስጥ በሚጫወተዉ ሚና ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚያደርግ የሚታወቅ ሲሆን ኦህዴድ በኢህአዴግ ዉስጥ የሚጫወተዉ ሚና የኦሮሞን ህዝብ ብዛት የማይመጥን ከሆነ የኦህዴድም ሆነ የኢህአዴግ የወደፊት እድል ከፊተኛ አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች በመናገር ላይ ናቸዉ። ከዚህ በተጨማሪ አዲሱ ጠ/ሚኒስትር ሀይለማሪያም ደሳለኝ የኦህዴድን ሙሉ ድጋፍ ሳያገኝ ምን ያክል ስራ መስራት እንደሚችል ብቻ ሳይሆን ለምን ያክል ግዜ በስልጣን ላይ መቆየት እንደሚችል አጠያያቂ እየሆነ መምጣቷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሀይለማሪያም ደሳለኝ ስልጣን ከያዘ የሰነበተ ቢሆንም እስካሁን ድረስ የራሱን ካቢኔ መመስረት ያልቻለዉ በኦህዴድና በህወሀት ዉስጥ በተፈጠረዉ የርስበርስ ልዩነትና ቁሬታ የተነሳ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

## ባራክ ኦባማ አሜሪካን ለሌላ አራት አመት የመምራት እድል ተሰጣቸዉ

ላለፉት ስድስት ወራት የአሜሪካንን ብቻ ሳይሆን የመላዉ አለምን ህዝብ ትኩረት የሳበዉ የአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት ምርጫ ባለፈዉ ማክሰኛ ምሽት በተቀማጩ ፕሬዚዳንት በባራክ ኦባማ አሸናፊነት ተጠናቀቀ። በዚህ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር በወጣበትና ባለፉት 30 አመታት ከተደረጉት ምርጫዎች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ፍክክርና የነቃ ተሳትፎ በተደረገበት ምርጫ ባራክ ኦባማ 303ቱን ኤሌክትራል ድምጽ በማግኘት ነበር የሪፓብሊካን ፓርቲ ተፎካካሪያቸዉን ሚት ሮምኒን ያሸነፉት። በአሜሪካ የፕሬዚዳንትነት ምርጫ አንድ ተወዳዳሪ ከተፎካካሪዉ ቀድሞ 270 ኤሌክትራል ድምጽ ካገኘ ምረጫዉን እንደሚያሸንፍ በህገ መንግስቱ ዉስጥ ተደንግጓል።

የሃምሳ አንድ አመት ጎልማሳ የሆኑትና የሁለት ሴት ልጆች አባት የሆኑት ባራክ ኦባማ ከኬንያዊ አባትና ከአሜሪካዊ እናት የሚወለዱ ሲሆን ነዉ አለም እየተባለ በሚጠራዉ በምእራቡ አለም የመጀመሪያዉ ጥቁር መሪ ናቸዉ። ባራክ ኦባማ የዛሬ አራት አመቱን ምርጫ አሸንፈዉ ስራ እንደጀመሩ ከአክራሪ ጽንፈኛ አሜሪካኖች ከፍተኛ ተቃዉሞ ደርሶባቸዉ በመጠኑም ቢሆን ከህግ አዉጭዉ አካል ጋር አብሮ የመስራት ችግር አጋጥሟቸዉ የነበረ ቢሆንም ሪፓብሊካኖች አሁንም ድረስ አምርረዉ የሚጠሉትን "ኦባማኬር" በመባል የሚታወቀዉን ስር ነቀል የጤና ህግ አርቅቀዉ ማስጸደቅ ችለዋል። የባራክ ኦባማን አመራርና የዲሞክራቲክ ፓርቲያቸዉን ርዕዮተአለም በመቃወም "ቲ ፓርቲ" የሚባል ጽንፈኛ ንቅናቄ ተፈጥሮ ባራክ ኦባማ በተወካዮች ምክርቤት የነበራቸዉን ከፍተኛ ድጋፍ ቢያሳሳዉም ፕሬዚዳንቱ የተነሱበትን አቅጣጫ ሳይስቱ በአላማቸዉ በመጽናታቸዉና ወጣቱን ህብረተሰብ፤ ሴቶችን፤ ሂስፓኒኮችንና ጥቁር አሜሪካዉያንን በሚገባ አቅፈዉ በመቅረባቸዉ በቀላሉ ለሌላ አራት አመት ሊመረጡ በቅተዋል። ዘንድሮ በተደረገዉ የአሜሪካ ፕሬዚዳንትነት ምርጫ ኢትዮጵያዉያን በያሉበት ከምርጫዉ በፊትም ሆነ በምርጫዉ ዕለት የነቃ ተሳትፎ ማድረጋቸዉን ከተለያዩ ምንጮች የተገኘዉ ማስረጃ ያመለክታል።

## የአሻንጉሊቱ "ፍርድ ቤት" ራሱን እንደገና አዋረደ!

የወያኔ አገዛዝ ከፍርድ ቤትት ወደ ተራ የፖለቲካ ማጥቂያ መሳሪያነት የለወጣቸዉ የኢትዮጵያ ፍርደ ቤቶች የዕለት ከዕለት ዉርደት አሁንም እነደቀጠለ ነዉ። ሃያ አመት ሙሉ አገዛዙ የወነጀላቸዉነ እየኮነነና አገዛዙ አሸባሪ ያላቸዉን በሽብርተኝነት ፈርጀ አስራትና የሞት ፍርድ ሲፈርድ የከረመዉ የወያኔዉ ፍርድ ቤት ከሰሞኑ ሙሉ ኃይሉን ወደ አሮሞ ህዝብ በማዞር የአርሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራቲክ ንቅናቄ (አፈሰዴን)ና የኦሮሞ ህዝብ ኮንግሬስ ፓርቲ ከፍተኛ አመራር አካል አባል የሆኑትን አቶ በቀለ ገርባንና አቶ ኦብላና ሌሊሳን አነግን ትረዳላችሁ የሚል ሰንካላ ምክንያት ፈጥሮ ወነጀለኛ አድርጓቸዋ ል። ወያኔ ሥልጣን ይዞ በቆየባቸዉ ባለፉት ሃያ አንድ አመታት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያደረሳቸዉንና አሁንም በማድረስ ላይ ያለዉን ግፍና መከራ የተቃወሙ የአሮሞ ልጆችን ህፃን፤ ሽማግሌ፤ ወንድና ሴት ሳይለይ እያሰረ አገሪቱን እስር ቤቶች በኦሮሞ ልጆች መሙላቱን ቀድሞ አባላቱ ሳይቀሩ የመሰከሩት ሐቅ ነዉ። አሁን ደግሞ ይህ አልበቃ ብሎት የህዝብን የነፃነት ፍላጎት ለማፈን ሆን ብሎ ያወጣቸዉን ህጎች መበጠቀም እሱ እራሱ ህጋዊ ብሎ በፈቀደዉ መንገድ የሚነቀሳቀሱ ፓርቲ መሪዎችን ሽብርተኛ በሚል የአሉባልታ ክስ ወንጀለኛ አድርጓቸዋል።

ባለፈዉ አመት በእነ እስክንድር ነጋና አንዱአለም አራጌ ላይ አሁን ደግሞ በአቶ በቀለ ገርባና በአቶ ኦብላና ሌሊሳ ላይ የወያኔ ፍርድ ቤት ያስተላላፈዉ "ሽብርተኛ" ናችሁ የሚል የፍርድ ዉሳኔ የሚያመለክተዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ ለመብት፤ለነፃነትና ለእኩልነት መታገል በሽብርተኝነት የሚያስከስስ መሆኑን ነዉ፤ ወይም ከወያኔ አባላትና ከትቂት ለሆዳቸዉ ካደሩ ባንዳዎች ዉጭ ያለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ቀን እየጠበቀ ሽብርተኛ ተብሎ መወንጀሉ የማይቀር መሆኑን ነዉ።

የኦሮሞ ህዝብ በሚኖርበት ቦታ የቆዳ ስፋትም ሆነ በህዝብ ብዛት በኢትዮጵያ ዉስጥ ትልቁን ቦታ የያዘ ህዝብ ነዉ። ይህ ታላቅ ህዝብ ዛሬም እንደትናንቱ ቁጥሩንና ብዛቱን በሚመጥን ልክ በአገሪቱ የፖለቲካ፤የኤኮኖሚና የማህበራዊ መስኮች ተሳትፎ በማድረግ ባለመቻሉ በገዛ አገሩ እንደ ሁለተኛ ዜጋ ተቆጥሮ የበይ ተመልካች ሆኗል። ይህንን አስከፊ ሁኔታ ለመለወጥ የሚታገሉትን የኦሮሞ ልጆች ደግሞ ወያኔ በድህንነት ሀይሎቹ ብቻ ሳይሆን የአገሪቱን ፍርድ ቤቶች ጭምር በመጠቀም ሽብርተኛ የሚል ታርጋ በመለጠፍ እያሰራቸዉ ነዉ። ለምሳሌ ባለፈዉ ሳምንት በሽብርተኝነት የተወነጀሉት አቶ በቀለ ገርባና አቶ አብላና ሌሊሳ የተወነጀሉት የአነግ ተባባሪዎች ናችሁ በሚልና ለሂውማን ራይት ተቋማት መረጃ ሰጥታችኋል በሚል የፈጠራ ክስ ነዉ። በሌላ በኩል ደግሞ ከመለስ ዜናዊ ህልፈት በኃላ በተደረገዉ የስልጣን ዝዉዉርና ሽግሽግ የአህዴድ አባላትን ከዋና ዋና የስልጣን ቦታዎች በማራቅ ወያኔ አሁንም በኦሮሞ ህዝብ ላይ የጀመረዉን የንቀት ዘመቻ እንደቀጠለበት ነዉ። በተለይ በቅርቡ የ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩ በአቶ ጁነዲን ሳዶ ባለቤት ወ/ሮ ሀቢባ መሐመድ ላይ የተመሰረተዉ የሽብርተኝነት ክስ የሚያሳየው በኦሮሞ ህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል ብቻ ሳይሆን ወያኔ ተጠግተዉት በከፍተኛ አመራር ቦታ ላይ ያስቀመጣቸዉን ሰዎችም ቢሆን አንገታቸዉን ደፍተዉ እስካልተገዙለት ድረስ ከመርካቶ እንደሚገዛ አላቂ ዕቃ ከተጠቀመባቸዉ በኃላ እንደሚወረዉራቸዉ ነዉ።

የህሊና እስረኞቹ ፍርደ ገምድል ውሳኔ ሲሰጣቸው ከቶ ሳይደናገጡ ጀግነነት በተሞላበት ለወያኔ ዳኞች የተናገሩት ምላሽ "እናንተ ለምትሰሩት የበደልና ፍርድቤቱን የማዋረድ ስራ ታሪክና ትውልድ ይጠይቃችኋል" በሚል ነው ስለዚህ ሁላችንም ከነዚህ የህሊና እስረኞች ብርታትና ጥንካሬ ብዙ ልንማር እንችላለን። ጀግኖችን በርቱ ማለትም የእኛ ፈንታ ነው።

በጥቅሉ በኦሮሞ ወገኖቻችን የሚደርሰው ማለቂያ የሌለውን በድል አብረን ልንታገለው ይገባል። የመብት ረገጣን በሚቃወሙ፣ የመልካም አስተዳደርን መመስረት በጠየቁ፣ ስለዲሞክራሲያዊ ስርአት መመስረትን ባነበነቡ የኦሮሞ ተወላጆች በእነ አቶ በቀለ ገርባ የተወሰነው የጥፋተኝነት ውሳኔ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ነው። አሻንጉሊቱም ፍርድ ቤት ተብየው ራሱን ከወያኔ መጠቀሚያነት ሊያጸዳ ይገባል፤ ለዚህም ምስክር እነ አቶ በቀለ ከይስሙላው የአእምሮ ድሃ ዳኛው ለተሰጣቸው የፍርድ ማቅለያ እድል እንዲናገሩ ሲሰጣቸው "ላልሰራነው ወንጀል እና እናንተ ላቀነባበራችሁት ፈጠራ መልስ እንደማይሰጡ ነገር ግን ታሪክ የማይረሳው ስራ መስራታቸውን ገልጸው እናንተ ለምትሰሩት የበደልና ፍርድቤቱን የማዋረድ ስራ ታሪክና ትውልድ ይጠይቃችኋል የሚል መደምደሚያ ሰጥተዋል። በመጨረሻም ሁላችንም በአንድ ድምጽ ወያኔ በኦሮሞው ወገናችን የሚያደርሰውን አዋርዶ የመግዛት እና የአሻንጉሊቱን ፈርደ-ገምድል ውሳኔ ልንቃወመውና ልንታገለው በቃህ ልንለው ይገባል!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ከፋፋዩ ወያኔ አዲስና ማደናገሪያ የእስልምና ምክር ቤት ማቋቋሙን ገለጸ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላለፉት አስራ አንድ ወራት በተከታታይ ያቀረቡለትን የሙብትና የነጻነት መከበር ጥያቄ ወደ ጎን በመተዉ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ፍላጎት ዉጭ ምርጫ አካሂዶ አዲስ የእስልምና ምክር ቤት ማቋቋሙን ገለጸ። በአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝና በኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ መካከል አንድ አመት ሙሉ ለዘለቀዉ አለመግባባት ዋናዉ ምክንያት የሙስሊሙ ማህበረሰብ የራሱን መሪዎች እሱ በሚፈልገዉ መንገድና ቦታ መምረጥ አለመቻሉ መሆኑ በግልጽ ይታወቃል። ሆኖም ወያኔ በአንድ በኩል የሙስሊሙ ማህበሰብ ያቀረበዉን ጥያቄ በሚገባ አስተናግጃለሁ እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የእስልምና ምክር ቤት አባላት ሙሉ በሙሉ በአገዛዙ ካድሬዎች ቁጥጥር ስር እንዲመረጡ ማድረጉ ኢትዮጵያዉያን የእስልምና እምነት ተከታዮችን እንዳስቆጣና የጀመሩትን ትግል አጠናክረዉ እንዲቀጥሉ የገፋፋቸዉ መሆኑን ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና አስረዳ።

የወያኔ የዜና ማሰራጫ አዉታሮች አዲስ የእስልምና ምክር ቤት መቋቋሙን ይፋ ያደረጉት የወያኔዉ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን የመበት ጥያቄ ሲያስተባብሩ በነበሩት "የመፍትሄ አፈላላጊ" ኮሚቴ አባላት ላይ የሽብርተኝነት ክስ በመሠረተ ማግስት መሆኑ ሙስሊሙን ማህበረሰብ በይበልጥ እንዳስቆጣዉ አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገኙት ዘጋቢዎቻችን የላኩልን ዜና ያስረዳል። የኢትዮጵያ እስልምና እምነት ተከታዮች ወያኔ መሪዎቻቸዉን ካሰረ በሁዋላ መብታችን ይከበር ከሚለዉ ዋናና መሠረታዊ ጥያቄያቸዉ ሌላ መሪዎቻችን በአስቸኳይ ይፈቱ የሚል ጥያቄም ሲያቀርቡ መቆየታቸዉ የሚታወስ ነዉ።

የወያኔ የዜና ማሰራጫዎች አዲስ የእስልምና ምክር ቤት መቋቋሙን ለህዝብ ይፋ ያደረጉት የወያኔዉ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን የሙብት ጥያቄ ሲያስተባብሩ የነበሩት "የመፍትሄ አፈላላጊ" ኮሚቴ አባላት ላይ የሽብርተኝነት ክስ በመሠረተ ማግስት መሆኑ ሙስሊሙን ህብረተሰብ በይበልጥ እንዳስቆጣዉ አዲስ አበባና በየክልሉ የሚገኙት ዘጋቢዎቻችን የላኩልን ዜና ያስረዳል። በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ዘገባ መሠረት በቅርቡ በወያኔ ቁጥጥር ስር በተካሄደዉ የምክር ቤት ምርጫ የእስልምና ምክር ቤቱ አባላት ከአዲስ አበባ፤ ከድሬደዋና ከዘጠኙ ክልሎች የተወከሉ መሆናቸዉን ለማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት ሳኡዲ አረቢያ ዉስጥ በሚገኘዉ የኢትአጵያ ኤምባሲ ዉስጥ በዋና ጸሀፊነትና በቢሮ ሀላፊነት ሲያገለግሉ የነበሩት ሼክ መሀመድ አማን የምክር ቤቱ ሊ/መንበር ሆነዉ የተሰየሙ ሲሆን ሼክ መሀመድ አማን የተወከሉት ከአሮሚያ ክልል መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በንዲህ እያለ አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በህጋዊ መንገድ መብታቸውን ለማስከበር ስለተንቀሳቀሱ በማንአለብኝነት እስር ቤት የወረወራቸውን ኢትዮጵያዊያን ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲለቃቸው ዓለምአቀፉ የሰብዓዊመብት ተሟጋች ድርጅት አምነስቲ ኢንተርናሺናል ጠየቁዋል። ድርጅቱ እንዳለው እስር ቤት የተወረወሩት ግለሰቦች ምንም እንኳን ሽብርተኛ የሚልና ሌሎች ቅጽሎች ቢለጠፉባቸው የጠየቁት የሙብት ጥያቄ ራሱ ወያኔ እገለገልበታለሁ የሚለውን ህገ መንግስት ጨምሮ በየትኛውም ዓለምአቀፍ ህግ ሊያስጠይቃቸው የሚችል አይደለም። የወያኔ አገዛዝ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ላነሳቸው ህጋዊ ጥያቄዎች አንዴም እንኳን ሰላማዊና ህጋዊ ምላሽ ለመስጠት አለመሞከሩን የጠቀሰው ድርጅቱ ይህ ደግሞ ወያኔ ከህዝብ ለሚነሱ ማናቸውም ጥያቄዎች የሚሰጠው ምላሻቸው የሃይል ርምጃ መሆኑን የሚያመላክት ነው ብሏል።

## የቀደሞዉ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ትግራይን የእንዱስትሪ ክልል ለማድረግ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ የኤፎርት ኩባኒያዎች እንቅስቃሴ ደከም ብሎ ታይቶ ነበር ያለችዉ አዜብ መስፍን አሁን ግን የኩባንያዉ እድገት ተጠናክሮ መቀጠሉን ተናግራ መስፍን ኢንጅኔሪንግ በያዝነዉ አመት በሦስት እጥፍ ማደጉንና በሚመጣዉ አመት በአምስት እጥፍ እንዲያድግ ለማድረግ ዝግጅቱ መገባደዱን ገልጻለች። ከዚህ በተጨማሪ የዚሁ የኤፎርት ኩባኒያ ንብረት የሆኑት አልሜዳ ጨርቃጨርቅ፤ መሶብ ሲሚንቶና ሱር ኮንስትራክሺን ድርጅቶች በዚህ በያዝነዉ አመት ብቻ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር ትርፍ ማጋበሳቸዉን ተናግራለች። ኤፎርት ኩባኒያ ህወሀት የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ ከሚቆጣጠርባቸዉና ከተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ገንዘብና ጥሬ እቃ ወደ ትግራይ የሚያግዝበት ዋነኛዉ መሳሪያ ለመሆኑ በብዙ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ኤኮኖሚስቶች ተጠንቶ በተደጋጋሚ መዘገቡ ይታወቃል።

## ሰማዕታቶቻችንን ምንግዜም አንረሳቸዉም

“መስከረም ሲጠባ ህዳር ሲታጠን ያኔ አሳይሻለሁ አረማመዴን”

ይህንን ቆየት ያለ ስንኝ ማን እንደቋጠረዉ ባይታወቅም የሐምሌዉ ጨለማ፤ የነሐሴዉ ጭቃና ከሰኔ እስከ መስከረም የሚዘልቀዉ የእርሻ ላይ ዉሎ ከሌላ ማህበራዊ ኑሮ የነጠለዉ የኢትዮጵያ ገበሬ ለሚወዳት ፍቅረኛዉ የተቃኘዉ ቅኔ ይመስላል። ሰኔ በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ገበሬዉ መስከረም ላይ የሰቀለዉን ሞፈርና ቀንበር መልሶ የሚያወርድበት ወር ሲሆን መስከረም ደግሞ አምስት ወር ሙሉ የጨበጠዉን ሞፈርና እርፍ መልሶ የሚሰቅልበት ወር ነዉ።

አዎ... ሰኔ የክረምቱ መግቢያ መስከረም ደግሞ የአዴይ አበባ መፍኪያ ግዜ ነዉና መስከረምና ሰኔ ለኢትዮጵያ ገበሬ ብዙ የሚሉት ነገር አለ። ጠላትንና የአገር ልጅን ባዳና ወገንን የማይለዩትን የወያኔ አግዓዚን መትረየሶች ለሚያስታዉስ ኢትዮጵያዊ ደግሞ ሰኔ 1997ና ጥቅምት 1998 ቢያጥቡት በማይጠራ ቢፍቁት በማይደበዝዝ የጽልመት ትዝታ የተሞሉ ወራት ናቸዉ። በየአመቱ ሰኔና ህዳር በመጡ ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ ገላ እንደገተገፋ አጥር ይፈርሳል፤ ልቡ ነዳጅ እንደጨረሰ መኪና ቀጥ ይላል። በ1998 ዓም የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ የአዲስ አበባ ነዋሪ ህዳር ሲታጠን ለማሸተት ወይም ህዳር ሚካኤልን ለማክበር አልታደለም። በዘረኞች መትረየስ ልጆቹን የተቀማዉ የኢትዮጵያ ህዝብ በ1998ቱ ህዳር የታጠነዉ እሱ እራሱ ባጨሰዉ ዕጣን ሳይሆን በወያኔ አግአዚ የባሩድ ሽታ ነበር።

ዘመናዊቷ የአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ በልጆቻቸዉ ደም ደጋግመዉ ከታጠቡ የአፍሪካ መዲናዎች አንዷ ናት። አዲስ አበባ በ126 አመት ታሪኳ ዉስጥ ብዙ እሴይ የሚያሰኙ ብሔራዊ ድሎችን እንዳስመዘገበች ሁሉ ብዙ አንገት የሚያስደፉ ህዝባዊ እልቂቶችንም አስመዝግባለች። በእርግጥም አዲስ አበባ ክፉዉንም ደጉንም አስተናግዳለች። ሆኖም እቺ ታሪካዊ ከተማ ማርሻል ግራዚያኒ፤ ከኦሎኔል መንግስቱ ኃ/ማሪያምና ሹምባሽ መለስ ዜናዊ የፈጸሙትን አይነት እልቂት በታሪካ አይታም ሰምታም አታዉቅም። እነዚህን ሦስት ፋሺስቶች በንጹህ ኢትዮጵያዉያን ላይ የፈጸሙት ወንጀል የኢትዮጵያ ታሪክ ዝንተአለም የሚዘክረዉ የታሪክ ጠባሳ ነዉ።

ለመኪናና ለእግረኛ ደምቀዉ የተሰሩትን የፒያሳ፡ የካዛንቺስ፤ የመርካቶ፤ የአራት ኪሎና የስድስት ኪሎ መንገዶች ግራዚያኒ በኢትዮጵያዉያን ደም ሲያጥበዉ አዲስ አበባ ገና የ54 አመት ጎልማሳ ነበረች። ግራዚያኒ ይህንን አሰቃቂ እልቂት ከፈጸመ ከ41 አመታት በሁዋላ በ1969 ዓም እነዚሁ የአዲስ አበባ መንገዶች ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም ብለዉ የጠየቁ ወጣቶች ደም እንደ ዉሀ ፈሰሰባቸዉ። ይህ ከሆነ ከ14 አመት በኋላ ወያኔ ደርግን አሸንፎ አዲስ አበባም የሠላምና የእድገት እንጂ የእልቂት ከተማ እንደማትሆን ቃል ተገብቶ ነበር። ሆኖም ደም እያፈሰሰ ስልጣን ላይ የወጣ ስልጣን ላይ መቆየት የሚችለዉ ደም እያፈሰሰ ነዉና በ1997 ዓም እነዚያ ደም የለመዱት የአዲስ አበባ መንገዶች በሽብሬ ደሳለኝ፤ በየሱፍ አብደላ፤ በነቢዩ አለማየሁ፤በፈቃዱ ነጋሽ፤ በአብርሃም ይልማ፤ በዙልፋ ሱሩር፤ በትንሳኤ ዘገየ፤ በሀብታሙ ቶላ፤በቢንያም ደገፋ፤በቃሲም አሊ፤ በቴዎድሮስ ግደይ፤ በረጋሳ ፈይሳና በሌሎችም ቁጥራቸዉ በበዛ ንጹህ ኢትዮጵያዉያን አስከሬን ተሸፈኑ። ለወትሮዉ የጥቅምት አበባ ሽታ የሚያዉዳት አዲስ አበባ በልጆቿ ደም ሽታ ታወደች። ከክረምቱ ብርድና ጨለማ የተገላገለዉን የአዲስ አበባ ነዋሪ ቤት የሞት ጽላሎት ሞላዉ። ኢትዮጵጵያ በሀዘን ተዋጠች። የኢትዮጵያ ህዝብ በንጹህ ልጆቹ ሞት ወያኔና አግዓዚ ደግሞ ያሰቡትን ያክል ባለመግደላቸዉ ሁለቱም አዘኑ።

ወያኔና አግዓዚ ወደዱም ጠሉ፤ፈለጉም አልፈለጉ የኢትዮጵያ ህዝብ እነሱ በፈጠሩት ዘረኛ ስርዐት ከርሰ መቃብር ላይ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መገንባቱ አይቀርም። ሆኖም “ዲሞክራሲ” የምንለዉ ጽንሰ ሀሳብ ከምርጫ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ስለሆነ ኢትዮጵያ ዉስጥ ምርጫ በተካሄደ ቁጥር የኢትዮጵያ ህዘብ የ1997ቱን ምርጫ ምን ግዜም ቢሆን ማስታወሱ አይቀርም። በተለይ ሰኔና ጥቅምት በመጡ ቁጥር ልጆቻቸዉን ያጡ ወላጆችና ወላጆቻቸዉን በአግዓዚ ጥይት የተነጠቁ ወጣቶች ልብ በኃዘን ይሞላል። የ1997ቱ ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ በብዙ ሺ አመታት ታሪኩ ዉስጥ ዲሞክራሲን ለመጀመሪያ ግዜ ያጣጣመበትና ነፃነትና ዲሞክራሲ የሚያስከፍሉትን መስዋዕትነት ተረድቶ ዉድ ልጆቹን ለሙብቱና ለነፃነቱ የገበረበት ታሪካዊ ምርጫ ነዉ።

ምርጫ 1997ትን ተከትሎ ወያኔ ሰኔና ጥቅምት ላይ የጨፈጨፋቸዉ ዜጎቻችን ጉዳይ በተነሳ ቁጥር የሚያንገበግበንና የሚቆጨን የንጸህ ዜጎቻችን ሞት ብቻ ነዉ ብለን የምናስብ ካለን እጅግ በጣም ተሳስተናል። የ1997ቱና የ198ቱ ግድያ “እኛና” “እነሱ” በሚል ጥላቻ፤ቂም በቀልና ዘረኝነት ላይ የተመሰረተ ግድያ ነዉ። ይህ ግድያ ከንጉስ ሄሮድስ በኃላ ለመጀመሪያ ግዜ ህፃናት ወላጆቻቸዉ ፊት የተገደሉበት አሰቃቂ ግድያ ነዉ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ይህ ግድያ በ1700 አመታት የክርስትና ታሪካችን ዉስጥ ለመጀመሪያ ግዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርሰቲያን ባሩድ ከሚተፉ መትረየሶች ለማምለጥ የተጠጓትን ልጆቿን አላዉቃችሁም ብላ በሮቿን የዘጋችበት የጨለማዉ ታሪካችን አካል ነዉ።

ዛሬ እኛ ኢትዮጵያዉያን የሰማዕታት ቀን ብለን የምንጠራዉን የዬካቲት 1928ቱን እልቂት፤ የ1969ኙን የኮሎኔል መንግስቱ እልቂትና የህዳር 1998ቱን እልቂት የሚለያያቸዉ ነገር ቢኖር የመጀመሪያዉ በነጭ ፋሺስቶች ሁለተኛዉና ሦስተኛዉ ደግሞ አገር በቀል በሆኑ ጥቁር ፋሺስቶች መፈጸማቸዉ ብቻ ነዉ። ፋሺስት ግራዚያኒ ከ30ሺ በላይ ኢትዮጵያዉያንን በአንድ ጀምበር ቢጨርስም የእነዚያ ጀግኖች ኢትዮጵያዉያዉያን ደም በከንቱ ፈስሶ አልቀረም። በመጋቢት ወር 1933 ዓም ግራዚያኒና አግበስብሶት የመጣዉ ወራሪ ጦሩ በጀግኖች አባቶቻችን ተሸንፎና ዉርደት ተከናንቦ ኢትዮጵያን ለቅቆ ወጥቷል። የማይነካና የማይደፈር ይመስለን የነበረዉ ኮሎኔል መንግስቱም ለእግሩ ጫማ በሌላዉ ጦር ተሸንፎ ከአገር ሸሽቶ ወጥቷል። የንጹህ ኢትዮጵያዉያንን ደም አፍስሶ ዛሬም ድረስ ዜጎችን እያሰረ፤ እየደበደበ፤ እየገደለና ከአገር እንዲሰደዱ እያደረገ የእጁን ሳያገኝ ተዝናንቶ የሚኖር ኃይል ቢኖር ወያኔ ብቻ ነዉ። አዎ! ዛሬ ኢትዮጵያ የምትመራዉ ልባቸዉ በጥላቻና በተሞላና እጃቸዉ በወንድሞቻችንና በእህቶቻችን ደም በተጨማለቀዉ ጨካኝ ዘረኞች ነዉ።

እኛ ኢትዮጵያዉያን ዶጋሌ፤ አድዋና፤ ማይጮዉ ላይ የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉ ጀግኖቻችንን ለዘለአለም እንደምናስታዉሳቸዉ ሁሉ ወያኔ የጨፈጨፋቸዉን ሰማዕቶቻችንንም ሁሌ እናስታዉሳቸዋለን። እነ ሽብሬ ደሳለኝ፤ ነበዩ አለማየሁና ቃሲም አሊ ግን ከእኛ የሚፈልጉት እንድናስታዉሳቸዉ ብቻ ሳይሆን እነሱ የተሰዉለትን አላማ ከግቡ እንድናደርስ ነዉ። አዎ! በአስራ ሁለትና በአስራ ስድስት አመት ለጋ ዕድሜያቸዉ ግንባራቸዉን ለአግዓዚ ጥይት የሰጡት የነቢዩ አለማየሁና የቢንያም ደገፋ ሞት ለእኛ ህይወት የሚሆነዉ የወያኔን ዘረኛ ስርአት ደምስሰን ኢትዮጵያ ዉስጥ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት መገንባት ከቻልን ብቻ ነዉ፤ አነነቢዩም ወደታች ዝቅ ብለዉ በተመለከቱን ቁጥር ለካስ አልሞትንም ብለዉ የሚዝናኑት የእነሱ ሞት የኢትዮጵያ ትንሳኤ ሆኖ ሲያዩት ብቻ ነዉ።ስለሆነም ዛሬ ሰማዕታቶቻችንን በምናስታዉስበት ወቅት ትልቁ ትኩረታችን ወደኋላ የማንመልሰዉ የወገኖቻችን ሞት ሳይሆን ፊት ለፊታችን ላይ ያለዉና በጅምር የቀረዉ እነሱ የቆሙለት አላማ ነዉ። ዛሬ እነነቢዩ ከእኛ የሚጠብቁት ኃዘን ሳይሆን እኛም እንደነሱ ነፃነቴን ወይም ሞቴን ብለን የመጨረሻዉ መስመር ላይ “ዘረኝነት በቃ” ብለን እንድንቆም ነዉ።

## በቅርቡ ፌዴራል ፖሊስ ወሎ ዉስጥ የወሰደዉ እርምጃ የወያኔን ጦር መከፋፈሉ ተሰማ

የወያኔ ፖሊስ በቅርብ ቀን በአማራ ክልል ቃሉ ወረዳ ገርባ ቀበሌ ዉስጥ የወሰደዉን ፋሽስታዊ እርምጃ በመቃወም በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዉስጥ ከፍተኛ ክፍፍል መፈጠሩን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ወታደራዊ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች ለግንቦት ሰባት ድምጽ ሬድዮ ዝግጅት ክፍል በላኩት መረጃ ገለጹ።

የፖሊስ ተግባር ህብረተሰቡን መጠበቅ ነዉ እንጂ ህዝብ ህገ መንግስቱ የሚሰጡወን መብት ተጠቅሞ ጥያቄ በጠየቀ ቁጥር ማሰር ወይም መግደል አይደለም በሚልና . . . የለም ፖሊስ ህገመንግስቱን ለማስጠበቅ የፈለገዉን እርምጃ መዉሰድ ይችላል በሚሉ መሠረታዊ ልዩነቶች ላይ ተመርኩዞ የተነሳዉ ብጥብጥ ሠራዊቱን ከላይ አስከታች ለሁለት እንደከፈለዉ ዉስጥ አዋቂ ምንጮቻችን አክለዉ በላኩልን መረጃ ገልጸዋል። ፖሊስ ህግመንግቱንና ህገመንግስታዊ ስርአቱን ለመጠበቅ ማንንም ሰዉ መግደል ወይም ማሰር ይችላል ብለዉ በአንደኛዉ ጎራ ከተሰለፉት የሠራዊቱ አባላት ዉስጥ ከ95 በመቶ በላይ የሚሆኑት የትግራይ ተወላጆች መሆናቸዉን የደረሰን መረጃ አመልክቷል። ትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ መኮንኖችንና ከፍተኛ ወታደራዊ አዛዦችን ማዕከል በማድረግ የተመሰረተዉ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከዚህ ቀደምም በተለያዩ አጋጣሚዎች ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ የሚወስዳቸዉን ፀረ ህዝብ እርምጃዎች በመቃወም ጎራ ለይቶ የተፋተገ ቢሆንም ይህ ከሰሞኑ በሠራዊቱ ዉስጥ የሚታየዉ መከፋፈል ግን በይዘቱም ሆነ በቅርጹ ከማንኛዉም ግዜ የተለየ መሆኑን ጉዳዩን በቅርብ በመከታተል ላይ የሚገኙ ምዕራባዉያን ወታደራዊ ጠበብቶችም በመናገር ላይ ናቸዉ። አንድ የግንቦት ሰባት ሬዲዮ ዝግጅት ክፍል በስልክ ያናገራቸዉ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የምዕራብ ዲፕሎማት በሰጡት መረጃ መሠረት ከዚህ ቀደም መከላከያ ሠራዊቱ ዉስጥ እንደዚህ አይነት የመከፋፈል አደጋ ሲከሰት መለስ ዜናዊ በፍጥነት ሁኔታዎችን ተከታትሎ ያበርድ እንደነበር ገልጸዉ አሁን ግን እንደዚህ የሚያደርግ ሰዉ ባለመኖሩና የገዢዉ ፓርቲ አስኳል የሆነዉ ህወሀት እራሱ ዉስጥ መከፋፈል ስላለ የኢትዮጵያ ሁኔታ እጅግ በጣም የሚያስፈራ ደረጃ ላይ ደርሷል ሲሉ ዲፕሎማቱ የተሰማቸዉን ስጋት ገልጸዋል።

## ቃሊቲ እስር ቤት ዉስጥ በግንቦት 7 በሚጠረጠሩ እስረኞች ላይ የሚደርሱ ግፍ መበርከቱ ተነገረ

የወያኔ አገዛዝ የተለያየ የፈጠራ ክስ እየመሰረተ እስር ቤት የሚያጉራቸዉን ዜጎች የየእስር ቤቱ ሀላፊዎች በግንቦት 7 አባላነት እየጠረጠሩ ከፍተኛ ግፍና መከራ እንደሚያደርሱባቸዉ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) የቃሊቲ ምንጮቹን ጠቅሶ ዘገበ። የወያኔ ካድሬዎችና የደህንነት ሠራተኞች ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ይሰራሉ በሚል እየጠረጠሩ የሚያስሯቸዉን ዜጎች በተለይ የአማራ ተወላጆችን የእስር ቤት ሃላፊዎች እንደሚያበድቧቸዉና ኢሰብአዊ ድርጊቶች እንደሚፈጽሙባቸዉ ለማወቅ ተችሏል። ይህ ተጠርጣሪ እስረኞችን የማሰቃየቱ እንቅስቃሴ በየእስር ቤቱ የሚታይ ቢሆንም በከፍተኛ ደረጃ ጎልቶና ተንሰራፍቶ የሚታየዉ ቃሊቲ እስር ቤት ዉስጥ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

ከዚህ ቀደም በእነ ጀኔራል ተፈራ ማሞ መዝገብ በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ተከሰው በእስር ላይ በሚገኙት ወታደራዊ መኮንኖች ላይ እጅግ ኢሰብዓዊ የሆነ አሰቃቂ ድብደባ የተፈጸመባቸው መሆኑን የግንቦት ሰባት ድምጽ በወቅቱ በተደጋጋሚ መዘገቡ የሚታወስ ነዉ። በወቅቱ የወያኔ አገዛዝ ቃሊቲ ዉስጥ በእረኞች ላይ የሚያደርሰዉ ይህ ነዉ የማይባል ሰቆቃ አለማቀፍ ትኩረትን በመሳቡ፣ በቃሊቲ የነበረው ሁኔታ በአንጻራዊ መልኩ ተሻሽሎ የነበረ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በእነ አቶ አንዱአለም አራጌ መዝገብ በተከሰሱትና በሌሎችም የፖለቲካ እስረኞች ላይ የሚደርሰው እንግልት እየጨመረ መምጣቱ ታውቋል።

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ስም በተነሳ ቁጥር የሚባንነዉ የወያኔ አገዛዝ የንቅናቄዉን እንቅስቃሴዎች በተለያዩ መንገዶች ለማደናቀፍ ይህ ነዉ የማይባል የተለያዩ ሙከራዎችን ቢያደርግም ይህ የቀን ቅዠቱ በፍጹም ሊሳካለት አልቻለም።

## ኢትዮጵያ ዉስጥ የአደንዛዥ ዕፅ ምርቶች መጠን በየአመቱ እየጨመረ መሆኑ ተነገረ

ኢትዮጵያ ዉስጥ በተለያዩ ክልሎች ካናቢስ በሚል መጠሪያ የሚታወቀው አደንዛዥ ዕፅ ምርት መጠን ከአመት ወደ አመት እየጨመረ መምጣቱን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኘዉና አፍቃሬ ወያኔ የሆነዉ ሬድዮ ፋና መዘገቡ ታወቀ። በሬድዮ ፋና ዘገባ መሰረት የአደንዛዥ ዕፅ ምርቱ እድገት ጎልቶ የሚታየዉ በአዲስ አበባ ለመልሶ ማልማት በታጠሩ አካባቢዎች፤ በደቡብ ክልልና ፣ በኦሮሚያ ክልል (ምስራቅ ሀረርጌ) አካባቢዎች መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ ባለፈው ዓመት ብቻ መጠኑ ከ400 ኪሎ ግራም በላይ የሆነና እንዲሁም ክብደቱ በዉል ያልታወቀ 8 ቁምጣ የካናቢስ እፅ በፖሊስ ክትትል መያዙን ሬድዮ ፋና ከፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን የተገኘዉን መረጃ በመጥቀስ ዘግቧል። በተለይ በሻሸመኔ አካባቢ በ1400 ስኩየር ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የተተከለ ካናቢስ መገኘቱንና ይህንን በተመለከተ ፌዴራል ፖሊስ ሃያ ተጠርጣሪ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ማዋሉን ለማወቅ ተችሏል።

የአደንዛዥ ዕጾችን ምርትና አጠቃቀም በተመለከተ ኢትዮጵያ ዉስጥ የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ባለፉት ሃያ አመታት ኢትዮጵያ ዉስጥ ጫት፤ ካናቢስ፤ ሀሺሽና ኮኬይንን የመሳሰሉ አነቃቂና አደንዛዥ ዕጾችን አዘዉትረዉ የሚወስዱ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጦቷል። የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሀኒትና የጤና እንክብካቤ ቁጥጥር ባለስልጣን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች ለአደገኛ ዕፅና ሌሎችም ሱሶች መጋለጣቸዉን በጥናት አረጋግጧል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከስራ እጦት፣ ተስፋ ከመቁረጥና ከራእይ እጦት የተነሳ ለአደጋኛ እጾች አቀላሉ እንደሚጋለጡ ጥናታዊ ዘገባዎቹ ያሳያሉ።

## በስደት ላይ የሚገኘዉ ሲኖዶስ ወያኔ አዲስ ፓትሪያሪክ ለመሾም የሚያደርገዉን ሩጫ አወገዘ

በህጋዊዉ ፓትሪያሪክ በብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የሚመራዉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በሐይማኖት ጉዳዮች ዉስጥ ጣልቃ እየገባ በፓትሪያሪክ ላይ ሌላ ፓትሪያሪክ ለመሾም የሚያደርገዉን ስዉር ደባ አጥብቆ እንደሚቃወም ገለጸ። ስደተኛዉ ስኖዶስ ይህንን አቋሙን የገለጸዉ ሰሞኑን የተካሄደዉ የሲኖዶሱን 34ኛ መደበኛ ጉባኤ ሲፈጸም ባወጣዉ መግለጫ ነዉ። ሲኖዶሱ በመግለጫዉ ላይ ጨምሮ እንደገለጸዉ ለሁለት የተከፈለችዉ ጥንታዊቷ ቤ/ክርስቲያን አንድነት የሚረጋገጠዉና ቤ/ክርስቲያኒቱ በሠላም መንፈሳዊ ስራዎቿን መስራት የምትችለዉ በህጋዊ መንገድ ተመርጠዉ ቅዱስ ሲኖዶሱን ሲመሩ የነበሩት አባ መርቆሪዮስ ወደ መንበራቸዉ ሲመለሱ ብቻ መሆኑን በግልጽ አስቀምጧል። የቤ/ክርስቲያኒቱን መሪዎች የመሾም ሀላፊነት የቤ/ክርስቲያኒቱ ብቻ ነዉ ያለዉ ይኸዉ መግለጫ አዲስ አበባ ዉስጥ ያሉት አባቶች የህጋዊዉን ፓትሪያርክ ወደ መነበራቸዉ በመመለሱ ጉዳይ የሚስማሙ ከሆነ አንድ እግዚአብሔርን የምታገለግለዉ ቤ/ክርስቲአናችን፤ ካህናቶቿና ምዕመናኗ አንድ ይሆናሉ በማለት ብፁዕ አቡነ መርቆርዮስ ወደ መንበራቸዉ እንዲመለሱ ጠይቀዋል።

በአንድ በኩል የሐይማኖት ነፃነት ተረጋግጧል እያለ በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱን የሐይማኖት መሪዎች እሱ እንዳሰኘዉ የሚሾመዉ የወያኔ አገዛዝ ከሃያ አመት በፊት በፓትሪያሪክ ላይ ሌላ ፓትሪያሪክ በመሾሙ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን፤ ካህናቱና ምዕመኑ ለሁለት ተከፍለዉ መቀየታቸዉ የሚታወስ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ወያኔ በአቡነ መርቆሪዮስ ቦታ በህገወጥ መንገድ ያስቀመጣቸዉ አቡነ ጳዉሎስ እንደ ሃይማኖት አባት ብቻ ሳይሆን እንደፖለቲካ ካድሬም ሆነዉ በማገልገላቸዉ የካህናቱንና የምዕመኑን መከፋፈል በይበልጥ እንዳባባሰዉ ለማወቅ ተችሏል።

ኢትዮጵያ ዉስጥና ከኢትዮጵያ ዉጭ የሚገኙትን ሁለቱን ሲኖዶሶች አንድ ለማድረግና አባቶችን ለማስታረቅ የሚደረገዉ ጥረት አሁንም እንደቀጠለ ሲሆን በሁለቱ ሲኖዶሶች መካከል ያለዉ መሠረታዊ ልዩነት ህጋዊዉ ፓትሪያሪክ ማን ነዉ የሚለዉ ጥያቄ መሆኑን በሁለቱም ወገን ያሉ አባቶች ተናግረዋል። በፓትሪያሪክ ላይ ሌላ ፓትሪያሪክ መሾም የማይታሰብ ነዉ የሚል ጠንካራ አቋም ያለዉ በስደት ላይ የሚገኘዉ ሲኖደስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክርስቲያን የሠላምና የአንድነት ጉባኤ የቀረበለትን የሠላም ጥሪ ተቀብሎ ተደራዳሪ ልዑካኑን መርጦ ለመላክ በዝግጅት ላይ መሆኑን ገልጿል።

## ኢትዮጵያ በለየላቸው ዘራፊዎች እጅ መውደቋን ሪፖርተር ጋዜጣ አጋለጠ

የወያኔ መንግስት ውስጡ በመሸጉ ሌቦች የተሞላ፣ በሙስና የተጨማለቀ፣ አቅመ ደካማ ሹማምንት የታጨቁበት፣ ለሀገር ከማሰብ ይልቅ ከሀገር የሚዘረፈው ሀብት ይበልጥ የሚያሳስበው የበሰበሰ ስርዓት መሆኑን በመጠቆም ስርዓቱ እድሜውን ማራዘም ከፈለገ አፋጣኝ መፍትሄ መፈለግ እንዳለበት አፍቃሪ ወያኔ የሆነው ሪፖርተር አስጠነቀቀ።

ሪፖርተር ጋዜታ ወያኔን ለማስጠንቀቅ በጻፈው በዚህ ጽሁፍ የወያኔ አገዛዝ በውስጡ የመሸጉ ሌቦች እንዳሉ ቢያውቅና ቢያምንም በተግባር ግን ሌቦቹን ለማጽዳት ርምጃ እየወሰደ አይደለም፤ እናም እነዚህ የወያኔ / ኢህአዴግ አባላት ሌቦች፣ በእጅጉ እየተጠናከሩና ኔትወርካቸውን እያሰፉ ነው፤ እነዚህ ሌቦች ለሀገር ከሚሰጡት ጥቅም ይልቅ ሀገሪቱን በመዝረፍ የሚያደርሱት ጉዳት በእጅጉ ያመዝናል፤ የወያኔ መንግስት ደግሞ በህዝቡ ላይ የሚበረታውን ያህል እነኚህን ሌቦች ለማጥፋት ጥረት አያደርግም በመሆኑም ስርአቱ ለሌቦቹ መፈልፈል አመቺ ሁኔታ በመፍጠሩና ለማጥፋትም ሙከራ ባለማድረጉ ተጠያቂ ነው በማለት ገሃዱን እውነታ አሳይቷል።

ከዚህም ሌላ የወያኔ ስርዓት ሌሎችን የሚጠይቀውን የብቃት ማረጋገጫ ራሱ ለሚሰራቸው ስራዎች አያቀርብም ያለው ጋዜጣው የብቃት ማረጋገጫ የሌለው የፕሬስ ስራ፣ የብቃት ማረጋገጫ የማይሰጠውና ሲያስነጥሱ የሚፈርስ መንገድ፣መጸዳጃ ቤት የሌለው ሆስፒታል፣ተገቢውን የብቃት ማረጋገጫ የማያሟሉ ህንጻዎች ፣ የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ የውሃ ቧንቧዎች ፣ የቴሌፎን ኔትወርኮችንና የመሳሰሉትን ለአብነት አንስቶ ኦዲት የማይደረጉና ሪፖርት የማያቀርቡ የወያኔ ድርጅቶችና ብቃት የሌላቸው ሹማምንት ያሉት አገዛዝ መሆኑን በመግለጽ በአጠቃላይ የመንግስትነት ባህሪ የሌለው ፍጹም የበሰበሰ ስርአት መሆኑን አመላክቷል።

በተጨማሪም የወያኔ መንግስት በግሉ ዘርፍ ኢንቨስመንት ላይ በርካታ ህጎች ያወጣል፤ ይሁንና የራሱን ኢንቨስትመንት፣ የራሱን በጀት አጠቃቀም፣ የራሱን የቃ ግዢ፣ የራሱን የጨረታ ሂደት፣ የራሱን የአፈጻጸም ሪፖርትና የመሳሰሉትን ግን አይቆጣጠርም በማለት አስረድቷል።

ሌሎችን ህግና መመሪያ ጣሳችሁ እያለ ሲያስርና ሲቀጣ የሚውለው ወያኔ ራሱ ህግ ሲጥስና መመሪያ ሲያወላግድ እንደሚውል ያነሳው ጋዜጣው ሌሎችን እየገመገሙና እየወረፉ የሚውሉት የወያኔ ተቋማት ህዝብ ቢገመግማቸው ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ የታያቸው አይመስልም ብሏል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**መካከኛ ሞገድ፡-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ፡-** በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎ ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org